# ሞጁል 4

## የአሰልጣኙ መምሪያ

## የማብዛት ተልዕኮ ስልጠና

### ጤናማ ቤተክርስቲያን መትከል

multiplication network

*more churches, stronger churches*

ትርጉም፤ ሚልኪያስ ለዕላጎ ሽምሱ - 2012

# የማብዛት ተልዕኮ

ጤናማ ቤተክርስቲያን ተከላ ሞጁል

መልቲፕሊኬሽን ኔትዎርክ ሚኒስተሪስ

ብዙ አጥቢያ ያላት/ ጠንካራ ቤተክርስቲያን

2007 ዓ.ም

ይህ የቤተክርስቲያን ተከላ አገልጋዮች ማሰልጠኛ ማኑዋል በAbridged Omega Course እና Multiplication Network Ministries' ጤናማ ቤተክርስቲያን መትከል የተሰኘ የማስተማሪያ መጽሐፍትን በማዋሃድ የተዘጋጀ ነው፡፡

MNM ከ Training Center for Church Planters እና ከ World Ministries ባገኘው ፈቃድ መሰረት ይህን ማስተማሪያ ለቤተክርስቲያን ጥቅም እንዲህ አቅርቦታል፡፡

እናንተም ይህን ማስተማሪያ ከዚህ በታች የተዘረዘሩትን መጠበቂያዎች እስከተከተላችሁ ድረስ ይህን መጽሐፍ እንድታባዙና እንድታሰራጩ ማበረታታችን የሰጠናችሁ ፈቃድ ይሁንልን፡፡

1. ለመጽሐፉ ጸሐፊያን እና ተርጓሚያን ዕውቅና መስጠት
2. መጽሐፉ ላይ ማሻሻያ አድርጋችሁ እንደሆነ እርሱን ማሳወቅ
3. ለማሳተሚያ ካወጣችሁት ዋጋ በላይ አለማስከፈል እና
4. ከ አንድ ሺህ ኮፒ በላይ አለማሳተም

ኦሜጋ ኮርስ፡-

ተግባራዊ የቤተክርስቲያን ተከላ አገልግሎት ማስተማሪያ

| | ለአንድ ቀን ስልጠና የጊዜ ድዘት እንደ ምሳሌ የቀረበ | |
|---|---|---|
| | የሞጁል አንድ መግቢያ | 2:00 |
| | የትምህርቱ ትኩረት መግለጫ፡- የጤናማ ቤተክርስቲያናት ስልታዊ መሰረቶች | 2:15 |
| | ሪፖርት ማቅረብ | 2:30 |
| ክፍለ ትምህርት አንድ | በእምነት መጽደቅ | 3:00 |
| | ረፍት | 4:00 |
| ክፍለ ትምህርት ሁለት | የመሪነት መጽሀፍ ቅዱሳዊ መርሆዎች | 4:15 |
| ክፍለ ትምህርት ሶስት | ወንጌል ስርጭት እና የቤተክርስቲያን ተከላ | 5:15 |
| | የምሳ ረፍት | 6:15 |
| ክፍለ ትምህርት አራት | የጥናት ቡድን መመስረት | 7:15 |
| ክፍለ ትምህርት አምስት | ወንጌል እና የማህበረሰቡን አስፈልጎት መድረስ | 8:15 |
| | የሻይ ረፍት | 3:15 |
| ክፍለ ትምህርት ስድስት | ከመጽሀፉ አሳብመውሰድ 3: የእግዚአብሔርን ቃል መተርጎም | 9:30 |
| | መዝጊያ | 10:30 |
| | የቀኑ ጥናት ፍጻሜ | 10:45 |

## መልካሙን ዜና ሳልሰሙ ማድረስ

### ሞጁል 4

### የትምህርቱ አላማዎች፡-

- ተሳታፊዎች በሐዋርያት ስራ መጽሐፍ ውስጥ የሚገኙትን አራቱን ቤተክርስቲያን የመትከል ምክንያቶች ለይተው ማውጣት ይችላሉ፡፡
- ተሳታፊዎች የመጽደቅን ስነመለኮታዊ ጽንሰ ሀሳብ በራሳቸው አገላለጽ ያስቀምጣሉ ደግሞም የመጽሐፍ ቅዱስ ትናት ቡድንን የመምራት ብቃታቸውን ተጠቀመው ሌሎች ጽንሰ ሀሳቡን እንዲረዱት ማርድረግ ይችላሉ፡፡
- ተሳታፊዎች አለማዊውን የመሪነት ጥበብ ከክርስቲያናዊው የመሪነት ጥበብ ጋር ማነጻጸር፤ በቤተክርስቲያን ተከላ ዙር ላይ ደግሞ አምስቱን የአዲስ ኪዳን የመሪነት ተግባራት መጠቀም፤ እንዲሁም በቤተክርስቲያን ተከላ ሂደት ላይ ከአዛዥ እና አመቻች የመሪነት አይነቶች ውስጥ የትኛው አግባብነት ያለው እንደሆነ ማስረዳት ይችላሉ፡፡
- ተሳታፊዎች ለቤተክርስቲያን ተከላ አገልጋዮች የተቀመጡትን አምስቱን የወንጌል ስርጭት መርሆዎች ይማራሉ ያስረዳሉም፡፡
- ተሳታፊዎች የመጽሐፍ ቅዱስ ጥናት ቡደንን ለመምራት የተተነተነ እቅድ ያዘጋጃሉ፡፡
- ተሳታፊዎች በወንጌል ስርጭት እና ግልጋሎት መካከል ያሉትን ሶስት አይነት ግንኙነቶች ይማራሉ፤ ለዚህ የሚረዳ ተግባራትንም ያደረጃሉ፡፡
- ተሳታፊዎች ከመልዕክቱ ሀሳብ በመውሰድ የመጽሐፍ ቅዱስ አጠናን ዘዴ ውስጥ መተርጎምን ይማራሉ፤ ይተገብራሉ፡፡
- ለሞጁል 5 በተቀመጠው የትግበራ እቅድ፤ ቀድመው የሰሩት ላይ በመጨመር እያንዳንዱ የቤተክርስቲያን ተከላ አገልጋይ የቤተክርስቲያን ለመትከል የሚያግዘውን መሪ እቅድ ያዘጋጃል፡፡ በተዘጋጀው ቅጽ ላይ እያንዳንዱ የቤተክርስቲያን ተከላ አገልግሎት ሰልጣኝ በጥናትና ምርምር ያገኘውን እና ቤተክረስቲያን የመትከል ጥረቱን ይደግፍልኛል ያለውን ግብአት በራዕይ፣ ተልዕኮ፣ እሴቶች እና ስልት ላይ ይጠቀምበታል፡፡ እያንዳንዱ የሰለጠነ የቤተክርስቲያን ተከላ አገልጋይ ከላይ ያሉትን ሁሉ አሟልቶ ከጨረሰ በኋላ ከመጋቢው ወይንም ድጋፍ ለማድረግ ከተስማማችው ቤተክርስቲያን (በመሪው ፊርማ እና በቤተክርስቲያኒቱ ማህተም የተረጋገጠ) የቤተክርስቲያን ለመትከል የሚያስችል መሪ እቅድ መሆኑን የሚያረጋግጥ ሰነድ ይሆናል፡፡

## የሞጁል 4 መግቢያ

### አሰልጣኙ መግቢያውን የሚያስተዋውቅበት ነጥብ (2 ደቂቃ)

- ተሳታፊዎችን ሞቅ ባለ፣ ፍቅር በተሞላ እና በሚያነቃቃ ሁኔታ የእንኳን ደህና መጣችሁ መልእክትህን አቅርብ
- ከዚያም በጸሎት የቀኑን ትምህርት ለእግዚአብሔር ክብር ይሆን ዘንድ አሳልፈህ ስጥ

### ዝምታን ለመስበር የሚከወን ተግባር፤ እኔ ማን ነኝ? (13 ደቂቃ)

ይህን ጨዋታ ለማጫወት መጀመሪያ በመጽሐፍ ቅዱስ የተዘገቡልንን ወይንም ሌሎች ታዋቂ ሰዎችን ስም በወረቀት ላይ በመጻፍ፤ ለጨዋታ የተመረጠው ሰው ጀርባ ላይ ትለጥፈዋለህ። ይህን ስታደርግ ተጫዋቹ የሚለጠፍለትን ስም በፍጹም ማየት የለበትም። ከዚያም ተሳታፊዎችን አንድ ጥያቄ ለአንድ ሰው ስለተለጠፈለት ሰው ማንነት እየጠየቀ ማንነቱን እስኪያውቅ ድረስ ይዞራል።

በጨዋታው መጨረሻ እያንዳንዱ ሰው እየተነሳ ለተሳታፊዎች የትኛው የመጽሐፍ ቅዱስ ገጸባህሪ እንደወከለ ይናገር። የደረሳቸው ገጸ ባህሪ ለቤተክርስቲያን ተካሳ ሊሆን የሚችል አንድ ባህሪ በመጥቀስ ለተሳታፊዎች እንዲያቀርቡ አድርጉ። ሁሉም ተሳታፊ አቅርቦ እንደጨረሰ ወደየስፍራቸው ይመለሱ እና በጋራ ጸልዩ።

# ስልታዊ መሰረት ለጤናማ ቤተክርስቲያናት (15 ደቂቃ)

የአሰልጣኙ መምሪያ መልሶ ምልከታ፡- ለእያንዳንዱ ስነመለኮታዊ አመክንዮ ማጣቀሻ የሚሆኑ ጥቅሶችን ለእያንዳንዱ ተሳታፊ በመስጠት፤ የደረሳቸውን የመጽሐፍ ቅዱስ ክፍል በየተራ እየተነሱ ለጠቅላላው ተሳታፊ እንዲያነብቡ አድርግ፡፡ ከምንባቡ ውስጥ የወንጌል ተልዕኮን ማዕከል ያደረገ መርህ የያዘን የመጽሐፍ ቅዱስ ክፍል እንዲለዩ እና በመማሪያ መጽሐፋቸው በዚህ ክፍለትምህርት ያለውን ክፍት ስፍራ በተገቢው ቃል እንዲሞሉ በማበረታታት ውይይቱን ምሩ፡፡

እንዲህ ብለህ ጠይቅ "በሞጁል 3 የተማርነውን "የስልት" ትርጉምን ማን ሊነግረኝ ይችላል?" (5 ደቂቃ)

**ትርጓሜ፡- ስልት፤** **ራዕያችሁን** እና **ተልዕኮአችሁን** ከግብ ለማድረስ **እሴቶቻችሁን** **በኑሮ** እየገለጣችሁ የምትተገብሯቸው **ተለይተው የሚታወቁ ተግባራት** ጥርቅም ነው፡፡

**የአሰልጣኙ መምሪያ፡-** እንዲህ በል "ቤተክርስቲያን በመትከል ሂደት ውስጥ መልካሙን ዜና ለሰዎች ለማድረስ ስልትን እንደ አንድ ተግባር ልናስበው እንችላለን፡፡"

ተሳታፊዎች ቀጥሎ ያለውን ተግባር በመማሪያ መጽሐፋቸው እንዲሞሉ አድርግ፡፡

**ቤተክርስቲያን የሚሆኑ የተለመዱ የስልት አመክንዮዎች፡-**

**የአሰልጣኙ መምሪያ፡-** ተሳታፊዎች ከታች በቀረበው ዝርዝር ውስጥ ያሉበትን አውድ የሚገልፀውን በመምረጥ በተቀመጠው ሳጥን ውስጥ ምልክት ያድርጉ፡፡

☐ የህዝብ ቁጥር በፍጥነት እያደገ ነው፡፡
☐ አዳዲስ ቤተክርስቲያናት ከነባር ቤተክርስቲያናት በበለጠ ሰዎችን በወንጌል ይደርሳሉ፡፡
☐ ነባር ቤተክርስቲያናት …….ወደመሆን አዘንብለዋል፡፡
☐ አዳዲስ ቤተክርስቲያናት ነባር ቤተክርስቲያናትን ለማነቃቃት ይጠቅማሉ፡፡

☐ ቤተክርስቲያናት የሚያስፈልጉት ወንጌል ባልደረሳቸው ሰዎች አካባቢ ነው፡፡

☐ አዳዲስ ቤተክርስቲያናት ለመቀየር ዝግጁ ናቸው (ግትር አይደሉም)፡፡

☐ በአንድ ቤተክርስቲያን ማህበረሰቡን ሁሉ መድረስ የማይቻል ነው፡፡

☐ አዳዲስ ቤተክርስቲያናት መሪዎችን በፍጥነት ያደራጃሉ፡፡

☐ .....ደቀመዝሙር ማድረግን ያግዛል፡፡

ከላይ ከተጠቀሱት የትኞቹን ምክንያቶች ነው እስከዛሬ አስበሃቸው የማታውቀው? የትኞቹስ ምክንያቶች ከአንተ ጋር ቤተክርስቲያን ተከላ አገልግሎት ላይ ለመሰማራት የሚፈልጉትን አገልጋዮች ያበረታታል?

______________________________________________________________________

______________________________________________________________________

____________________________________________________

**የአሰልጣኙ መምሪያ፡-** እንዲህ በል "እስኪ በአዲስ ኪዳን ዘመን የተተከሉ አንዳንድ ቤተክርስቲያናት የተተከሉበትን ምክንያት ከግምት ውስጥ እናስገባ፡፡"

**በአዲስ ኪዳን አንዳንድ ቤተክርስቲያናት የተተከሉበት ምክንያት፡-**

**የአሰልጣኙ መምሪያ፡-** ለእያንዳንዱ የቤተክርስቲያን ተከላ ምክንያትን የሚደግፉ የቤተክርስቲያን የመጽሐፍ ቅዱስ ክፍሎችን በማውጣት ለእያንዳንዱ ተሳታፊ አንዳንድ በማካፈል ለጠቅላላው ተሳታፊ ድምጻቸውን ከፍ አድርገው ያንብቡ፡፡ ከዚያም እያንዳንዱን ተሳታፊ ካነበበው ክፍል ቤተክርስቲያን የሚተከልበትን ምክንያት እንዲለዩና በመመሪያ መጽሐፋቸው ላይ በሚያገኙት ክፍት ቦታ ላይ ተገቢውን ቃል እንዲያሰፍሩ አድርግ፡፡

**አንብብ፡-** ሐዋ 8፡1-8፣ 12

**ስልታዊ አመክንዮ** 1፡- ለስደት የተሰጠ ምላሽ፡፡ ከኢየሩሳሌም ውጪ እንደተተከለ የተዘገበልን የመጀመሪያው ቤተክርስቲያን እንዲተከል የሆነበት ምክንያት ስደት ነው፡፡ ቤተክርስቲያን ተከላ እንዴት ለስደት ስልታዊ ምላሽ ሊሆን እንደሚችል ተወያዩ፡፡ ተሳታፊዎች በዚህ መንገድ የተከፈተ ቤተክርስቲያን ያውቁ እንደሆነ ከራሳቸው ወይንም ከሌሎች የሰሙትን እንደምሳሌ በመጠቀም ምላሽ እንዲሰጡ አበረታታ፡፡

**አንብብ** ሐዋ 10፡1-24፣ 36-48

**ስልታዊ አመክንዮ** 2፡- ለእግዚአብሔር ምሪት ምላሽ መስጠት፡፡ እግዚአብሔር ለቆርኔሌዎስ እና ለትሮስ በሰጠው የተለየ ምሪት እና የእነዚህ ሁለት ሰዎች ለእግዚአብሔር ምሪት ተገቢውን ምላሽ በመስጠታቸው ምክንያት በቂሳርያ ያለች ቤተክርስቲያን ልትተከል በቅታለች፡፡ እግዚአብሔር ለቆርኔሌዎስ እና ለጴጥሮስ እንዴት እንደተገለጠላቸው በሚከተሉት ጥያቄዎች መሰረት ተወያዩ፡- ከእነርሱ ጋር እየተነጋገረ የነበረው እግዚአብሔር መሆኑን በምን አወቀ? እግዚአብሔር የተለየ ምሪት እንደሰጠን በምን እናውቃለን? ተሳታፊዎች በዚህ መንገድ የተከፈተ ቤተክርስቲያን ያውቁ እንደሆነ ከራሳቸው ወይንም ከሌሎች የሰሙትን እንደ ምሳሌ በመጠቀም ምላሽ እንዲሰጡ አበረታታ፡፡

**ስልታዊ አመክንዮ** 3፡- ለሰዎች ግብዣ ምላሽ መስጠት፡፡ ጴጥሮስ ከቆርኔሌዎስ የቀረበለትን ግብዣ ተቀብሎ ቆርኔሌዎስ ቤት ሲገኝ እግዚአብሔር በቆርኔሌዎስ ቤተሰብ ያደረገውን መልካምነት ምስክር ለመሆን በቅቷል፤ ታዲያ ይህን የመንፈስ ቅዱስ ስራ በቆርኔሌዎስ ቤት መመስከቱ ይህ ግብዣ ከእግዚአብሔር የሆነ እንደሆነ በመንፈሱ እንዲረዳና እቅዱን ከዚህ መገለጥ ጋር እንዲያስተካክል እድል ሰጥቶታል፡፡ ተሳታፊዎች በዚህ መንገድ የተከፈተ ቤተክርስቲያን ያውቁ እንደሆነ ከራቸው ወይንም ከሌሎች የሰሙትን እንደ ምሳሌ በመጠቀም ምላሽ እንዲሰጡ አበረታታ፡፡

**አንብብ፡-** ሐዋ 16፡9-15

**ስልታዊ አመክንዮ 4፡-** <u>መልካሙን ዜና የማድረስ</u> <u>ታማኝነት ልማድ</u>። በፊሊጲስዩስ ያለች ቤተክርስቲያን ትተከል ዘንድ ምክንያት የሆነው የጳውሎስ በየደረሰበት መልካሙን ዜና የመናገር ታማኝነት ልማድ ነው። ጳውሎስ ወደ መቄዶንያ ለመሄድ በፊሊጲስዩስ ማለፍ ነበረበት፤ ታዲያ እግረመንገዱን፤ ወንጌልን ለማድረስ በነበረው ታማኝነት ልማድ በዚህ ከተማ ሊዲያ የተባለችን ሴት ይተዋወቃል፤ በእርሷም ትጋት ጳውሎስ ሌሎች አብያተክርስቲያናት በረከት ይሆን ዘንድ ከጎኑ የምትቆም ቤተክርስቲያን በዚያ ሊተከል ቻለ። ተሳታፊዎች በዚህ መንገድ የተከፈተ ቤተክርስቲያን ያውቁ እንደሆነ ከራቸው ወይንም ከሌሎች የሰሙትን እንደ ምሳሌ በመጠቀም ምሳሽ እንዲሰጡ አበረታታ።

**የአሰልጣኙ መምሪያ፡-**

- የሪፖርት ማቅረቢያውን ቅጽ በመጠቀም ተሳታፊዎች ከሞጁል 2 ማብቂያ ጀምሮ እስከዚህ ጊዜ ያሳቸውን ቤተክርስቲያን ተከላ ተግባራት እቅድ እንዲያቀርቡ እድል ስጥ።
- በዚህ ረገድ ከፍተኛ ውጤት ያስመዘገቡትን አመስግን፤ በዚህ ጉዳይ ተስፋ ወደመቁረጥ የቀረቡተን ደግሞ አበረታታ። ጊዜ የምታገኝ ከሆነ ጠቅላላውን ተሳታፊ፤ በትንንሽ ቡድኖች በመክፈል የቤተክርስቲያን ተከላን በተመለከተ አንዳችሁ ለሌላችሁ ጸልዩ።
- ሪፖርት የሚደረግበትን ሂደት በተመለከተ የሚነሱ ማንኛውም አይነት ጥያቄዎችን መልስ።

# የቤተክርስቲያን ተከላ ሪፖርት

ወርሃዊ ሪፖርት

## ጠቅላላ መረጃ

| ሪፖርቱ የተደረገበት ወር | | የምክርና ድጋፍ አገልግሎቱ ተከናውኗል | አዎን | የለም |
|---|---|---|---|---|

| | |
|---|---|
| የቤተክርስቲያን ተከላ አገልጋዩ ስም | |
| ቤተክርስቲያኒቱን የሚተክለው ሰው አካባቢ | |
| የአካባቢው አስተባባሪ | |

| **ግለሰቦች** | ወርሃዊ ግብ | ወርሃዊ ውጤት |
|---|---|---|
| በቅርቡ የተዋወቃቸው ሰዎች<br>ቤተክርስቲያን ለመትከል ታስቦ ወንጌልን ለማድረስ የተዋወቃቸው ሰዎች | | |
| ወደጌታ የመጡ አዳዲስ ሰዎች<br>የኢየሱስ ተከታዮች | | |
| በቅርብ የተጠመቁ ሰዎች<br>በጥምቀት ስርአት የተሳተፉ ሰዎች | | |
| በስልጠና ላይ ያሉ አዳዲስ መሪዎች<br>ለቤተክርስቲያን ተከላ የሚመለመል ሰው ለመሪነት የሰለጠነ ነው | | |

**አነስተኛ ቁጥር ያላቸው ሰዎች የሚሳተፉበት ቡድን| በትንሹ ሁለት ደቀመዝሙር እና አንድ መሪ**

| | ወርሃዊ ግብ | ወርሃዊ ውጤት |
|---|---|---|
| አዳዲስ ትናንሽ ቡድኖች<br>በዚህ ወር የተጀመሩ ቡድኖች | | |
| በትናንሽ ቡድኖች የተካተቱ አዳዲስ ተሳታፊዎች<br>በዚህ ወር በትናንሽ ቡድኖች መሳተፍ የጀመሩ አዳዲስ ሰዎች | | |
| የቡድን መሪ የሆኑ አዳዲስ መሪዎች<br>በቤተክርስቲያን ተከላ አገልጋዩ ክትትል የሚደረግለት ቡድን መሪ የሆነ አዲስ መሪ | | |

## የጸሎት ርዕስ

1. ______________________________
2. ______________________________
3. ______________________________

## ምስክርነት

ከዚህ በታች ያለው ክፍት ቦታ የመጨረሻ ሳይሆን እንደመነሻ የቀረበ ሲሆን ተጨማሪ ወረቀት መጠቀም ይቻላል

______________________________

______________________________

______________________________

______________________________

# ክፍለትምህርት 1

# በእምነት መጽደቅ፡-

# ከእግዚአብሔር ጋር ሳለን ህብረት መሰረት (60 ደቂቃ)

**የአሰልጣኙ መምሪያ፡-** ከታች ያለውን መጽሐፍ በመጠቀም ተሳታፊዎች ጽድቅን ማዕከል ያደረገ ጭብጥ ያለው ጥናት፤ ከክፍሉ መልዕክት መውሰድ የመጽሐፍ ቅዱስ ጥናት ዘዴን በመጠቀም እንዲያጠኑ አድርግ፡፡ በዚህም በመማሪያ መጽሐፋቸው ላይ ያለውን ክፍት ስፍራ በተገቢው ቃላት እንዲሞሉ እና ጽድቅን በራሳቸው አገላለጥ እንዲጽፉ አድርግ፡፡

መግቢያ፡- (10 ደቂቃ)

እንዴት ነው እግዚአብሔርን በቅርበት እና ፍቅርን በተሞላ ህብረት ልናውቀው የምንችለው?

በእርግጥ እግዚአብሔር ተቀብሎናል?

በእግዚአብሔር ፊት ያለን ተቀባይነት ከወዴት የመጣ ነው?

እንዴትስ ነው እርሱን ደስ የሚያሰኝ ኑሮ የምንኖረው?

ኃጢአት በምንሰራበት ወቅት ምን እንሆናለን?

ሚላርድ ኤሪክሰን የተባለ ክርስቲያን የስነመለኮት ምሁር እንዲህ ጽፏል፡-

*ስለጽድቅ የሚነሱ አስተምህሮዎች የአንድ ሰው በእግዚአብሔር ፊት የመቆም ብቃት ጋር የተቆራኙ ነው፡፡ ግለሰቡ ሁኔታ ከወንጀለኛነት፤ ከወንጀል ነጻ ወደመሆን መለወጥ አለበት፡፡ ይህም የሚሆነው ግለሰቡ በእግዚአብሔር ፊት ጻድቅ እንደሆነ ሲፈረድበት እና አምላክ የሚፈልገውን መስፈርት እንደሚያሟላ ተደርጎ ሲታይ ነው፡፡ ይህን ለመግለጥ የምንጠቀምበት የስነመለኮት ቃል ጽድቅ የሚለው ነው…ጽድቅ አንድ ዳኛ አንድን ተከሳሽ ከወንጀል ነጻ እንደሆነ እንደሚደነግግ ሁሉ፤ እግዚአብሔርም አንድ ሰው ጻድቅ እንደሆነ የሚደነግግበት ሂደት ጽድቅ ይባላል፤ በተመሳሳይ ዳኛ ተከሳሽን ከተከሰሰበት ክስ ፍጹም ነጻ እንደሆነ እና ከተከሰሰበት ክስ ተቃራኒ ያለ ንጽህና ማንነቱ እንደሆነ እንደሚፈርድ ሁሉ…ጽድቅም ከክርስቶስ ጋር አንድ ከመሆናችን ጋር በጥብቅ የተቆራኘ ነው፡፡*

**የመጽሐፍ ቅዱስ ጥናት (10 ደቂቃ)**

1. ጽድቅ በእነዚህ የሚገኝ አይደለም

    ሀ. <u>በስራ</u>

    ለ. እግዚአብሔር ኃጢአታችንን <u>ከቁብ ስለማይቆጥረው</u> እንደፈለግን እንድንኖር

2. ጽድቅ እንዲህ ነው

    ሀ. የእግዚአብሔር <u>ጽድቅ</u>፤ ሮሜ 3፡21-24

    ለ. ታላቁ <u>ልውውጥ</u>፤ 2ቆሮ 5፡21፤ኢሳ61፡10፤ ሮሜ 4፡3-5፤ 8፡1፤ኤፌ 4፡22-24

3. በእምነት የመጽደቅ ዋናው ጉዳይ

ሀ. ራሳችንን ማጽደቅ እንችላለን?

ለ. እግዚአብሔር ስለሰራው ስራ እኛ ምስጋናውን መውሰድ እንችላለን?

**ምሳሌ፡- (30 ደቂቃ)**

አንድ ሰው በህግ ፊት ሞት የሚያስቀጣ ጥፋት አጥፍቶ ቀረበ እንበል፤ ታዲያ ይህ ሰው የሞት ፍርድ ፍጻሜውን እየጠበቀ ባለበት ወቅት የሰውዬው ጓደኛ ወደዳኛው ቀርቦ ሰውዬው ነጻ እንዲወጣ ይጠይቃል፡፡ በዚህ ጊዜ ዳኛው የሰውዬውን ጓደኛ "አንድ ልጅህ በእርሱ ቦታ እንዲሞት ከፈቀድክ እለቀቀዋለሁ" አለ፡፡ የሰውዬውም ጓደኛ "ይህ የማይረባ ሀሳብ ነው፤ እንዴት እንዲህ ያለውን አስቸጋሪ ነገር የማደርገው?"፤ ዳኛው ግን በአቋሙ በመጽናት "ከዚህ ሌላ ሰውዬውን የምለቅበት ምንም አይነት መንገድ የለም" አለው፡፡ ከብዙ ጭንቅ በኋላ አባትየው እጅግ እያዘነ አንድ ልጁን በጓደኛው ፋንታ እንዲሞት ወሰነ፤ ምክንያቱም ጓደኛውን የሚያድንበት መንገድ ይህ ብቻ እንደሆነ ስለተረዳ፡፡ ልጁም የአባቱን ትዕዛዝ በማክበብ ወደ ዳኛው በመሄድ በአባቱ ጓደኛ ቦታ ለመሞት እንደተስማማ ይነግረዋል፡፡ በቀጣዩ ቀን አንዳኛው የሰውዬው ልጅ ላይ የሞት ቅጣቱን በማስፈጸም የሰውዬውን ጓደኛ ነጻ ያወጣዋል፡፡ ከጥቂት ጊዜ በኋላ በአንድ አጋጣሚ ከሞት ፍርድ ነጻ የወጣው ሰው ከሌላ ጓደኛው ጋር እንዴት ከሞት ፍርድ እንዳመለጠ ሲነግረው ልጁን በእርሱ ቦታ እንዲሞት የፈቀደው አባት ይሰማዋል፡፡ "እንዴት ነው ከሞት ፍርድ የተረፍከው?" ተብሎ ለቀረበለት ጥያቄ፤ ሰውዬው እንዲህ ነበር የመለሰው፤ " ደህና...እዮህ በእስር ቤት ውስጥ እያለሁ ራሴን በንጽሕና እጠብቅ ነበር፣ በጣም ጥሩ ባህሪም ነበረኝ ከዚህም በተጨማሪ ጠባቂዎቹ የሚሉኝን ሁሉ እፈጽም ነበር፤ በዚህም ጥሩ ምግባሬ ነጻ ሰው እንዲሆን ተፈረደልኝ፡፡"

**ለውይይት የሚረዱ ጥያቄዎች፡-**

- ይህ ጓደኛው ለተናገረው ንግግር የልጁ አባት ምን አይነት ምላሽ የሚሰጥ ይመስልሃል?
- የጓደኛው ልጅ ነፍሱን ከሰጠ በኋላ የዚህ ሰው መልካም ምግባር እርሱን ከእስር ለማስፈታት ምን አይነት አስተዋጽዖ ያደርጋል?
- በእያንዳንዱ ቀን ከክርስቶስ ጋር ባለን ህብረት፤ ለምንድን ነው በጸጋ የጀመርነውን ጉዞ በጸጋ ወይንም ክርስቶስ በመስቀል ላይ በጨረሰው ስራ ለመቀጠል እጅግ ከባድ የሚሆንብን?
- በእምነት መጽደቅ እንዴት ነው ከእግዚአብሔር ጋር ያለህ ህብረት ላይ ምን አይነት እንድምታ ይኖረዋል፤ እግዚአብሔርም ከአንተ ጋር የሚያደርገው ህብረት ምን አይነት እንደሆነ የምታስበውን አሳብ ይወስናል?

**አሳብህን ግለጥ፡- (10 ደቂቃ)**

ከዚህ በታች ባለው ክፍት ቦታ፤ "በእምነት መጽደቅ" ምን ማለት እንደሆነ የራስህን ትርጓሜ አስፍር።

## ለሞጁል 5 የሚሆን የትግበራ እቅድ

ወደ ሞጁል 5 ከመሻገራችሁ በፊት አንተ ወይንም ሌላ አንድ ሰው በመምረጥ፤ በእምነት ስለመጽደቅ ከመልዕክቱ አሳብ የመውሰድ የጥናት ዘዴን ተጠቅማችሁ ካጠናችሁ በኋላ በግል ወይንም በቡድን ስለጽድቅ የራሳቸውን ትርጉም ይጻፉ። ከዚያም የጻፉትን ለሚቀጥለው ክፍለትምህርት ይዘው ይምጡ።

## ክፍለትምህርት 2

# መጽሐፍ ቅዱሳዊ መርህ ለመሪነት (60 ደቂቃ)

**የመሪነት ትርጓሜ፡- (10 ደቂቃ)**

**የአሰልጣኙ መምሪያ፡-** እንዲህ በል "መሪነት የሚለውን ቃል ለመተርጎም ጥቂት ጊዜ ውሰዱ ከዚያም በተቻለ መጠን ጥቂት ቃል በመጠቀም ከታች ባለው ስፍራ ላይ ትርጓሜአቸውን በመማሪያ መጽሐፍህ ላይ ባለው ክፍት ስፍራ አስፍር፡፡"

መሪነትን እንዲህ እተረጉመዋለሁ፡-

---

---

---

እንዲህ በል "አብሯችሁ ሲሰራ የሚችል አጋር ፈልጉና አንዳችሁ የሌላችሁን ትርጓሜ አንብቡ፡፡"

ከዚህ በታች የቀረቡትን አሳቦች ሁሉም ተሳታፊ በጋራ ይወያይባቸው፡-

- "መሪነት <u>ተጽዕኖ ፈጣሪነትን</u> ነው፤ አንድ ሰው በሌሎች ላይ ተጽዕኖ የመፍጠር ችሎታ ካለው መሪ ነው፡፡" (Sanders, *Spiritual Leadership,* p. 31)፡፡
- "መሪነት አንድ ሰው እግዚአብሔር የሰጠውን በሰዎች ላይ ተጽዕኖ የመፍጠር አቅም ተጠቅሞ የእግዚአብሔርን ህዝብ <u>እግዚአብሔር ወዳየላቸው</u> ዓላማ የማድረስ በየጊዜው የሚለዋወጥ ሂደት ነው፡፡" (Clinton, *Making of a Leader,* p. 14; cf. p. 127)፡፡
- ከላይ ያነሳናቸው ሁለት ጸሐፍት ካነሱት የመሪነት ትርጉም ጋር እናንተ የሰራችሁትን ትርጉም አስተያዩ፡፡
- መሪነት በአንድ ቃል እንዲተረጎም ቢፈለግ ሊሆን የሚችለው "<u>ተጽዕኖ</u>" ነው፡፡
- መሪነትን "ተጽዕኖ" ብለን ስንተረጉም ምን ያመለክተናል?

- በቤተክርስቲያናችሁም ሆነ በምታገለግሉበት የአገልግሎት ዘርፍ ውስጥ ተጽዕኖ ፈጣሪ ሰዎች እነማን ናቸው?

## የመጽሐፍ ቅዱሳዊ መሪነት መርህ (5 ደቂቃ)

አለማዊ መሪነት ብዙውን ጊዜ "እነርሱ የሚመሩቸው ሰዎች የሚጠበቅባቸውን ስራ ይሰራሉ ብለው አያምኑም" እንደውም "ሰዎችን በጣም የምታምናቸው ከሆነ አንተን እንደመጠቀሚያ ያደርጉሃል" ብለው ያስባሉ፡፡ እንዲህ ያሉ መሪዎች በእነርሱ ስር ያሉ ሰዎች መሪው የሚፈልገውን የሚሰሩት፤ መልካም የሰሩትን በመሸለም እና በትክክል ያልሰሩትን በቅጣት በማስፈራራት እንደሆነ ይናገራሉ፡፡ ከዚህም የተነሳ አለማዊ መሪዎች ስልጣንን በያዙት የመሪነት ስፍራ ወይንም ከግለሰቡ ማንነት በሚመነጭ የመፈጸም ብቃት የሚመጣ ነው ብለው ያምናሉ፡፡ እንዲህ ያለው የመሪነት አይነት በዓለምም ሆነ በቤተክርስቲያን ሲገኝ ይችላል፡፡

### ሰባቱ የስልጣን ምንጮች

ከዚህ በታች የምንመለከታቸው ሰባቱ የስልጣን ምንጮች ናቸው፤ ሁሉንም ጥሩም መጥፎም የሚያደርጋቸው አጠቃቀማችን ነው፡፡ ራስህን ከእነዚህ ውስጥ በየትኛው መሪነት አይነት ትመድበዋለህ?

- ቀደታ/ በአንድ ስራ ስረጅም ጊዜ መስራት - ጊዜን መሰረት ያደረገ
- ስልጣን - አንድ ሰው ባለው ማዕረግ
- ብቃት - በአንድ ሰው ተፈጥሮአዊ ችሎታ ላይ መሰረት ያደረገ
- ፍርሃት - በፍርሃት እና ሽልማት ላይ መሰረት ያደረግ
- አክብሮት - በባህሪ እና ማንነት ላይ መሰረት ያደረገ
- መረጃ - ስነገሮች ባለ ቀርበት እና ዕውቀትን መሰረት ያደረገ
- ወዳጅነት - በጓደኝነት ወይንም ትውውቅ ላይ መሰረት ያደረገ

**ምንጭ፡-** From “Creativity and Innovation in Leadership,” a doctoral class taught by Dr. Larry Osborne

## ውይይት፡- (25 ደቂቃ)

**የአሰልጣኙ መምሪያ፡-** ከዚህ በታች የቀረበውን ጽሑፍ በመጠቀም በአለማዊ እና በክርስቲያናዊ መሪነት መካከል ያለውን ልዩነት ለማወያየት ተጠቀም፡፡ ከዚህ በታች ከተሰጡት የመጽሐፍ ቅዱስ ክፍሎች ውስጥ የመሪነትን መርሆዎች ለመለየት ጊዜ ውሰድ፡፡ ታዲያ ውይይቱ በሚደረግበት ወቅት ተሳታፊዎች ከዚህ በታች ባለው ሰንጠረዥ ውስጥ ያለውን ክፍት ቦታ  በተገቢው ቃል እንዲሞሉ አድርግ፡፡

በጳውሎስ ዘመን በባሪያ እና ጌታ መካከል ያለውን ግንኙነት ከግምት ውስጥ በማስገባት፤ ኤፌ 6፡9 ላይ ካለው ክፍል በእኛ መሪነት ስር ያሉ ሰዎችን እንዴት መያዝ እንዳለብን እንገነዘባለን?

ከላይ ያነሳነውን አይነት ባህሪ በሚያንጸባርቁ መሪዎች ጥቃት ደርሶብህ ያውቃል? በምን መልኩ ተጽዕኖ ፈጠረብህ?

1. የመሪነት ስልጣን ከእግዚአብሔር ዘንድ የሚመጣ ነው፡፡

ከዚህ በታች ያሉ የመጽሐፍ ቅዱስ ክፍሎች፤ ስልጣን በእግዚአብሔር ዘንድ እንደሆነ ለማሳየት ምን ያስተምሩናል?

- የህዝብ አስተዳዳሪነት ተቀባይነት ያለው ስልጣን ነው (ሮሜ 13፡1-7፤ 1ጴጥ 2፡13-17)
- ቤተሰቡ (ኤፌ 5፡22-25፤ 6፡1-4)
- ቤተክርስቲያኒቱ (ዕብ 13፡17)
- የኢየሱስ ምሳሌ የሚሆን መሪነት (ዮሐ 8፡28-29)
- ክርስቲያን መሪዎች በእግዚአብሔር የተመረጡ ናቸው (ዮሐ 15፡16)

2. ክርስቲያን መሪዎች ትሁት አገልጋይ ናት ባህሪያቸው ሊሆን ይገባል፡፡

ከዚህ በታች የቀረቡት የመጽሐፍ ቅዱስ ክፍሎች ከአገልጋይነት በተቃራኒ ያሉ ባህሪያት ምን እንደሆኑ ይነግሩናል? መልስ ሊሆኑ ከሚችሉ ነገሮች አንዱ ትዕቢት ነው፡፡

- እግዚአብሔር ትዕቢትን ይጠላል (ምሳ 6፡16-17)
- የኢየሱስ ምሳሌ የሚሆን መሪነት (ፊሊ 2፡1-8፤ ዮሐ 13፡15)

3. ክርስቲያናዊ መሪነት ጥንቃቄ በተሞላ ጥናት እና ስምምድ ማደግ ይኖርበታል፡፡

- የእግዚአብሔር ቃል በትክክል ለማስተማር የሚያበቃ ትጋትን ማዳበር (2ጢሞ 2፡15)
- ሰውነትን መቆጣጠር (ሮሜ 6፡13፣ 1ቆሮ 6፡20)
- በፈተና መጽናት (ያዕ 1፡12)

***በአለማዊ እና በክርስቲያን መሪነት መካከል ያለ ልዩነት***

| አለማዊ መሪነት | ክርስቲያናዊ መሪነት |
|---|---|
| በራስ የሚታመን | በእግዚአብሔር የሚታመን |
| ሰዎችን የሚረዳ/የሚያውቅ | እግዚአብሔርን እና ሰዎችን የሚረዳ/የሚያውቅ |
| በራሱ የሚወስን | የእግዚአብሔርን ፈቃድ የሚፈልግ |
| በስራው ተስፋ የሚታመን | አገልጋይ የሚመስል |
| የራሱን ስልት የሚያደረጅ | የእግዚአብሔርን ስልት የሚፈልግ እና የሚከተል |
| ሌሎችን በማዘዝ የሚደሰት | እግዚአብሔርን በመታዘዝ የሚረካ |
| ራስ ተኮር በሆኑ ጉዳዮች የሚነቃቃ | ለእግዚአብሔር እና ለሰዎች ባለው ፍቅር የሚነቃቃ |
| ራሱን የቻለ | በእግዚአብሔር ላይ ጥገኛ የሆነ |

እንዲህ ጠይቅ፤ "ሰዎች ብዙ ጊዜ ስለ "ተፈጥሮአዊ መሪነት" ሲያወሩ "በአለማዊ መሪነት" ባህሪ ላይ መሰረት አድርገው ነው ወይንስ "በክርስቲያን መሪነት" ላይ?"

4. መጽሐፍ ቅዱስ ፈርጀ ብዙ የአመራር ዘይቤዎችን ይዘረዝራል፡፡

ኤፌ 4፡11-12 በአዲስኪዳን ቤተክርስቲያን ውስጥ ስለሚገኙ የተለያዩ የመሪነት ሚናዎች ይዘረዝራል፡፡ በመሆኑም እነዚህ አንዳቸው ከሌላቸው የሚለዩ የአመራር አይነቶች "የእግዚአብሔርን ህዝብ ለስራ ወይንም ለአገልግሎት" ማዘጋጀት የሚጠቀሙ ተግባራት ናቸው፤ ወይንም በሌላ አነጋገር የእግዚአብሔርን ህዝብ እግዚአብሔርንና አንዳቸው ሌላቸውን ለማገልገል እንዲችሉ ያስታጥቃሉ ማለት ነው፡፡

### *የአዲስ ኪዳን ቤተክርስቲያን መሪነት ተግባር*

| ስጦታ | ትኩረት | ተግበር |
|---|---|---|
| ሐዋርያ | ራዕይ | ግንባር ቀደም መሆን |
| ነብይ | ኃጢአት | ስብከት |
| ወንጌላዊ | ደህንነት | ያልዳኑትን መድረስ |
| መጋቢ | መንከባከብ | የዳኑትን ማሳደግ |
| መምህር | እውነት | ማስጠንቀቅ |

**የቡድን ውይይት፡-** (5 **ደቂቃ**)

**የአሰልጣኙ መምሪያ፡-** በሞጁል 1 "የቤተክርስቲያን ተከላ ዑር" በሚለው ርዕስ ስር የተመለከትናቸውን ተግባራት ዝርዝር በሰሌዳ ወይንም (በኢዝል easel ፓድ)[1] ጻፍ፡፡ ተግባራቱ ጸሎት፣ ወንጌል ስርጭት፣ ደቀመዝሙር ማድረግ፣ መሰባሰብ፣ መሪዎችን ማብቃት፣ መብዛት እና መንቀሳቀስ ናቸው፡፡ ከዚያም የተሳታፊው ቁጥር በዛ ያለ ከሆነ እንደሁኔታው በቡድን በመከፋፈል በእነዚህ የቤተክርስቲያን ተከላ ዑር ደረጃዎች የአዲስ ኪዳን መሪነት ተግባር እንዴት እንደሚያገለግል ተወያዩ፡፡

**ቀደም ብሎ የተጀመረውን የተሳታፊዎች የጋራ ውይይት ቀጣይ ክፍል፡-** (5 **ደቂቃ**)

5. የቤተክርስቲያን መሪነት ተቀዳሚ ተግባር <u>ማስታጠቅ</u> ነው፡፡

በኤፌ 4፡11-12 ያለው ክፍል የቤተክርስቲያን ተቀዳሚ ተግባር ምን እንደሆነ ይነግረናል?

[1] ትርጉም የሚያስፈልገው

## *አዛዥ እና አደባዳይ መሪነት*

| አዛዥ መሪነት | አደባዳይ መሪነት |
|---|---|
| ስራ ተኮር፡-<br>"ስራህን ፈጽም" | ሰው ተኮር<br>"ሰዎችን አሳትፍ" |
| ተግባር | ኃላፊነት ሰጪ |
| ግብ፡-<br>"የአገልግሎት ዘርፉን ስራ መስራት" | ግብ፡-<br>"ሴሎችን ለአገልግሎት ማስታጠቅ" |
| ተግባሩን በራሱ የሚከውን ሰራተኛ ነው | አስታጣቂ፣ አስቻይ፣ አሰልጣኝ ነው |

**የአሰልጣኙ መምሪያ:-** ይህን ጥያቄ ጠይቅ፤ "አዛዥ መሪነት ነው ወይንስ አደሳደይ መሪነት ለቤተክርስቲያን በበለጠ ጠቃሚ የሚሆነው?" ከተሳታፊዎች መካከል ፈቃደኛ የሆነ ሰው አዛዥ መሪነት የሚያስፈልግበትን ሁኔታ እንዲያብራሩ ጠይቅ፤ እንዲሁ አደሳደይ መሪነትም የሚያስፈልግበትን አጋጣሚ ለሚያብራራ ሌላ ሰው እድል ስጥ።

ማስታወሻ:- ሁለቱም የመሪነት ሌነቶች ለቤተክርስቲያን አስፈላጊ ናቸው። በአጠቃላይ አዛዥ መሪነት በአንድ ጉዳይ ምንም አይነት ዕውቀት የሌላቸውን ሰዎች ለማሳመራት እና ቢዚያም ውጤታማ እንዲሆኑ ለማስቻል ሲጠቅም፤ አደሳደይ መሪነት ደግሞ በአንድ ጉዳይ ላይ በቂ ዕውቀትና ልምድ ያላቸውን ሰዎች አንድን ጉዳይ እዲከውኑ ለማስቻል ይጠቅማል። የመሪነት ዘይቤ የሚወሰነው ልንሰራው በያዝነው ጉዳይ እና ስራውን ለመስራት በተዘጋጁት ሰዎች ዕውቀትና ልምድ ነው። ይሁን እንጂ፤ በማኛውም አይነት ዘይቤ የቀረቡ መሪነቶች አንድ የሚሆኑት ለእግዚአብሔርና ለሰው ባላቸው የፍቅር መንፈስ ነው።

## የግል አሳብን መግለጥ (10 ደቂቃ)

**የአሰልጣኙ መምሪያ:-** እያንዳንዱ ተሳታፊ ከዚህ በታች ያሉትን ጥያቄ በሚመለከት ያውን አሳብ እንዲገልጥ እና ከእያንዳንዱ ጥያቄ ስር ባለው ክፍት ስፍራ አሳቡን በጽሑፍ እዲያሰፍር አድርግ። ይህን ተግባር ከፈጸምክ በኋላ ከተሳታፊዎች የጥቂቶቹን መልስ ለጠቅላላው ተሳታፊ አንብብ።

- ባለህበት ባህል እንዴት ነው ሰዎች መሪ የሚሆኑት?

______________________________________________

______________________________________________

______________________________________________

______________________________________________

- ለምንድን ነው ሁሉም መሪዎች በመጀመሪያ ጥሩ ተመሪ መሆን ያለባቸው?

- እንዴት ነው አሁን "የያዝከው የመፈንት ስልጣን ከእግዚአብሔር እንደመጣ" ማወቅህ እንዴት የመፈንት አመለካከትህን ይቀይረዋል?

- ከአምስቱ የአዲስኪዳን መፈነት ተግባር ይበልጥ ከአንተ ተፈጥሮ ጋር የሚሄደው የትኛው ነው?

- እነዚህ መጽሐፍ ቅዱሳዊ የመፈነት መርሆች ከአለማዊ የመፈነት መርሆች በምን መንገድ ይለያሉ?

## የተሞክሮ ጥናት (10 ደቂቃ)

**የአሰልጣኙ መምሪያ፦-** ተሳታፊዎችን በቡድን በመክፈል ከዚህ በታች ያሉትን የተሞክሮ ጥናቶች በማካፈል፤ በደረሳቸው የተሞክሮ ጥናት ውስጥ መሪው የተገበረው ወይንም ያልተገበረው

የመጽሐፍ ቅዱሳዊ መርህ ምን እንደሆነ በጽሑፍ ያስፍሩ፡፡ ከዚያም እነርሱ መሪውን የማማከር እድል ቢያገኙ ምን አይነት ምክር ይሰጡት እንደነበር ይወስኑ፡፡ ከዚያም ሁሉም ተሳታፊ አንድ ላይ በመሆን እያንዳንዱ ቡድን ስለደረሰው የተሞክሮ ጥናትና ስለሰጡት ምላሽ ለጠቅላላው ተሳታፊ በማቅረብ ጥቂት የውይይት ጊዜ ይውሰዱ፡፡ ማስታወሻ፡- ከዚህ በታች የቀረቡትን ሁሉንም የተሞክሮ ጥናቶች መጠቀም ግድ አይደለም፤ እንደየ አስፈላጊነቱ በቡድን ቁጥራችሁ ልክ እና እናንተ ካላችሁበት አውድ ጋር የሚሄደውን ብቻ በመለየት መጠቀም ትችላላችሁ፡፡

1. ዮሴፍ ካምፓላ በምትባል ከተማ አንድ የቤተክርስቲያን ተከላ ፕሮጀክትን ይመራል፤ ታዲያ እርሱ በሚመራው ቡድን ውስጥ ሳራ እና ሩት የተባሉ ሁለት እህቶች ከሶስት ወር በፊት ተቀላቅለዋል፡፡ ይሁን እንጂ ከቅርብ ጊዜአት ወዲህ ሳራና ሩት በዚህ አገልግሎት ተስፋ ወደመቁረጥ እየተቃረቡ ያሉ ይመስላል፡፡ አነዚህ ሁለት ሰዎች ለወንጌል ስርጭት የሚሆን ምርጥ የሚባል አሳብ አላቸው፤ ነገርግን መሪያቸው የሆነው ዮሴፍ በፍጹም የእነርሱን አሳብ ለመስማት ፈቃደኛ አይደለም፡፡ አንኳን ሊሰማቸው ጭራሽ በየጊዜው ምን መስራት እንዳለባቸው እና እንዴት መስራት እንዳለባቸው ይነግራቸዋል፡፡ ትዕግስታቸው የተሟጠጠው ሳራና ሩት ይህን አገልግሎት ትተውለት ወጥተው ራሳቸው ሌላ ለማደራጀት እያሰቡ ነው፡፡ **የዮሴፍን መሪነት እንዴት ትገመግመዋለህ?**

2. ሮቤርቶ ማድሪድ በምትባል ከተማ የሚገኙ ቅዱሳን የመጽሐፍ ቅዱስ ጥናትን ይመራል፡፡ ሮቤርቶ እጅግ የሚደንቅ ስብከትን በየእሁዱ አምልኮ ፕሮግራም ይሰብካል፣ ከዚያም በሳምንቱ አጋማሽ ደግሞ የታማኝ ተሳታፊው ቁጥር አሁን ወደ 20 እየደረሰ ያለ የቤት ህብረት ይመራል፤ ሁሉም ሰው በሮቤረቶ የቃል እግዚአብሔር ዕውቀት እና ፕሮግራሞችን በማቀናጀት አቅሙ ይደመማል ይወደዋል፡፡ ይሁን እንጂ፣ ከቅርብ ጊዜ ወዲህ ሮቤርቶ ከስራ ብዛት የመጣ ከፍተኛ ድካም እየተሰማው ነው፡፡ ታዲያ ለዚህ መፍትሄ ብሎ ያሰበው እርሱ በሚመራው ቡድን ውስጥ

የሚገኘውን ሚካኤልን የተወሰኑትን የእርሱን ቡድን አባላት ከፍሎ ቡድን እንዲመሰረት እና እንዲያስጠና ነበር። ሆኖም ይህን ለማድረግ ሚካኤል ዝግጁ ስላልነበር፤ አዲስ ቡድን ለመመስረት ያላየው ፍላጎት ጥቂት ነበር። **ሮቤርቶ ለሚካኤል እንዴት ኃላፊነትን ለመስጠት እንደሞከረ ገምግሙ።**

3. ሎሬት በምትባል አንዲት ትንሽ ከተማ ከፍተኛ የሆነ የቤተክርስቲያን እድገት ይስተዋላል። አንዳንዶች የዚህ እድገት መነሻ አልፍሬዶ እና አን ድንቅ የመሪነት ብቃት እንደሆነ ይናገራሉ። አልፍሬዶ እና አን ይህን ቤተክርስቲያን የተከሉት አልፍሬዶ ከአንድ ሴሚናሪ በስነመለኮት ትምህርት የመጀመሪያ ዲግሪውን እንደተመረቀ ነበር። ታዲያ በዚህ ቤተክርስቲያን የነበሩ አማኞች በአብዛኛው አዳዲስ አማኞች ሲሆኑ ስለቤተክርስቲያን አመራር ምንም አይነት ዕውቀት አልነበራቸውም። አልፍሬዶ በየሳምንቱ ያለውን የእሁድ አምልኮ የስብከት ጊዜ ሲዝ አን ደግሞ ሰንበት ትምህርቱን ታደራጃለች። አገልግሎቱ እያደገ እና እየሰፋ በሄደ ቁጥር አፍሬዶ እርሱን የሚያግዙ ተተኪ መሪዎችን ለማግኘት ትኩረቱን የሚመራቸው ሰዎች ላይ ያደርጋል። ይሁን እንጂ አንድም ሰው ማግኘት አልቻለም ነበር። እንደመታደል ሆኖ፣ በአንድ መልካም አጋጣሚ ለቤተክርስቲያን መሪነት ሲሰጥኑ የሚችሉ ሶስት ወጣቶችን ያገኛል፤ ይህም ብቻ ሳይሆን ከሶስቱ ሁለቱ ሲማ በምትባል ከተማ ባለ አንድ የመጽሀፍ ቅዱስ ሴሚናሪ የሚማሩበትን የነጻ ትምህርት እድል ያመቻችላቸዋል፤ እና ከትቂት ጊዜ በኋላ ትምህርታቸውን ይጀምራሉ። **ይህን መሪዎችን የማብቃት ሂደት እንዴት ተመዝኑታላችሁ?**

4. እክባር በሚኖርበት በሰሜናዊ ህንድ አንድ ስፍራ ምንም አይነት የወንጌላውያን ቤተክርስቲያን አልነበረም። እናም አክባር አካባቢውን ሲያጠና፤ በዚህ አካባቢ ያሉ አማኞች ወደተለያዩ የአገሪቱ አካባቢዎች ቤተክርስቲያን ለመካፈል እንደሚጓዙ፤ እነደውም አንዳንዶቹ 30 ኪሎሜትር ያህል ተጉዘው እንደሚያመልኩ ተረዳ። በአክበር መሪነት በዚህ አካበቢ ያሉ አማኞች አንድ ቤተክርስቲያን መሰረቱ። እናም በመሰባሰባቸው እጅግ ደስ ያላቸው ሰዎች ቤተክርስቲያኒቱ እንዴት መደራጀት እና ማደግ እንዳለባት ሁሉም ይሄድበት የነበረውን ቤተክርስቲያን ተሞክሮ በማካፈል አሳብ ይሰጥ ነበር። ነገር ግን አክበር ሁሉም ከዚህ በፊት ከተለያዩ ቤተክርስቲያናት

የተማረትን ባህል እና አደረጃጀት እንዲረሱ እና እርሱ የአዲሲቱ ቤተክርስቲያን መጋቢ እደመሆኑ እርሱ የሚለውን ብቻ እንዲሰሙ በግልጽ ነገራቸው፡፡ **አክበር እየተጓዘበት ያለው አስተሳሰብ ምን የሚያስከትል ይመስላችኋል?**

5. ጃኪዩስ የተባለ አገልጋይ በምዕራባዊ ዑርኪናፋሶ በሚገኙ ሶስት የተለያዩ ከተሞች ቤተክርስቲያናትን ይተክላል፡፡ ይህ አገልጋይ በተፈጥሮ ቤተክርስቲያን ለመትከል ተሰጥኦ ያለው ነው፡፡ የወንጌላዊነት ስጦታ ያለው እንደመሆኑ ከሰዎች ጋር ለመግባባት የማይቸገር እና ወንጌልን ለማድረስ ከፍተኛ አቅም ያለው ነው፡፡ ጊታር እየተጫወተ እና እየዘመረ ታዳሚዎችን ለሰአታት ማዝናናት ይችላል፡፡ ነገሮችን መጀመር በጣም ይወዳል ስለዚህ ከአንዱ ወደሌላው ቶሎ ቶሎ ይቀያይራል፡፡ እርሱ የተከላቸው ቤተክርስቲያናት የእርሱን ባህሪ መልመድ የተቸገሩ ይመስላል፡፡ ምክንያቱም በመጀመሪያ እጅግ ደስ ብሏቸው ከእርሱ ጋር ይሆኑ እና ሌላ አዲስና አስገራሚ ነገር ሲጀመር ቀድሞ የያዙት ደስ አልል ይላቸዋል፡፡ ይህን ጃኪዩስ ራሱ ቢያውቅም ተፈጥሮው እንደሆነ በማመን ይህን በየትኛውም መንገድ ማስተካከል እንደማይችል ያምናል፡፡ ምንም እንኳን እርሱ እንዲህ ያለ ድካም ቢኖርበትም እግዚአብሔር በዚህ ድካሙም ቢሆን እንደሚሰራ ያምናል፡፡ የጃኪዩስን መሪነት እንዴት ትመለከቱታላችሁ?

6. ጆን ሲድኒ በተባለች በአውስትራሊያ በምትገኝ ከተማ ቤተክርስቲያን ለመትከል ብዙ ጥረት አድረጓል፡፡አሁን ላይ ቤተክርስቲያኒቱ ጥሩ በሚባል ሁኔታ ላይ ትገኛለች፡፡ በዚህ ሶስት አመት ውስጥ ብቻ ወደ 200 አባላት ያሉት ሆኗል፡፡ ባለቤቱ እና አራት ልጆቹ ጆንን ለቀናት ሳያዩት ሊያሳልፉ ይችላሉ፤ ምክንያቱም በለሊት ስለሚወጣ እና በጣም አምሽቶ ስለሚገባ፡፡ በእርግጥ እንዲህ ያለውን ኑሮ ጆን አይፈልገውም፤ ነገር ግን ከአባሉቹ አንዳንዶቹ ታማሚዎች አንዳንዶቹም ቤት አልባ ስለሆኑ በጊዜው እንዲጎበኛቸው እና ትኩረት እንዲሰጣቸው ይፈልጋሉ፡፡ ጆን እንዲህ ያለውን አገልግሎቱን ቢያቆም ቤተክርስቲያኒቱ እድገቷ እንደሚቆምና ሰዎችም እንደማይድኑ ያውቃል፡፡ ጆን ጥሩ መሪ ይመስልሃል? ነው ካልክ ለምን? አይደለምም ካልክ ለምን?

# ክፍለትምህርት 3

## ወንጌል ስርጭት እና ቤተክርስቲያን ተከላ (60 ደቂቃ)

**ለሞጁል 4 የሚሆን የተግበራ እቅድን ሪፖርት ማቅረብ** (30 ደቂቃ)

**የአሰልጣኙ መምሪያ፡-** 3 ወይንም 4 ሰዎችን አንድ ቡድን በማድረግ ሁሉንም ተሳታፊ በቡድን መድብ፡፡ ከዚያም እያንዳንዱ ተሳታፊ ለተመመደበት ቡድን አባላት ራዕዩ፣ ተልዕኮ፣ እሴት፣ እና ስልትን ከመጋቢው፣ ከእናት ቤተክርስቲያን እና በቤተክርስቲያን ተከላ ከእርሱ ጋር ከሚሳተፉ ግለሰቦች ጋር በሚወያይበት ወቅት ምን አይነት ምላሽ እንዳገኘ ያስረዳ፡፡ የትኛውን አሳቡን ተቀበሉለት? ለምን? እንዲሁም የትኛውን አሳብ እንዲሻሻል ወይንም እንዲቀየር ተደረገ? ለምን? ከትንንሽ ቡድኖች ውይይት በኋላ ጠቅላላውን ተሳታፊ ደግሞ በአንዳንድ ጉዳዮች ላይ እንዲሳተፉ አድርግ፡፡

**አምስቱ ቤተክርስቲያን ለመትከል ወንጌልን የምናሰራጭባቸው መርሆች** (20 ደቂቃ)

የአሰልጣኙ መምሪያ፡- ከዚህ በታች የቀረበውን አሳብ በመጠቀም ጠቅላላው ተሳታፊ ቤተክርስቲያን ለመትከል ስለሚደረግ ወንጌል ስርጭት መርሆች እንዲወያዩ አድርግ፡፡ ተሳታፊዎችም በመማሪያ መጽሐፋቸው ባለው ክፍት ስፍራ ተገቢውን ቃላት እንዲሞሉ አሳስባቸው፡፡

1. በሰዎች መካከል ያለን ተፈጥሮአዊ መስተጋብር ተጠቀም፡፡
   - ምን አይነት የህብረት መንገድ/መረብ ነው ኢየሱስ ተከታዮቹን ለመጥራት የተጠቀመው? ዮሐ 1፡40-41፤ 4፡28-30፣ ሉቃ 8፡38-39
2. አዳዲስ አማኞች እንደዳኑ ወዲያው ለሌሎች ወንጌልን ያደርሳሉ/ይመሰክራሉ፡፡

- ለምንድን ነው አዳዲስ አማኞች ውጤታማ የወንጌል ስርጭት አገልጋዮች የሚሆኑት? እንድትወያዩበት ጥቂት መልሶችን በዚህ አስፍረናል፦
    - እምነታቸው አዲስ/ትኩስ ስለሆነ
    - አዳዲስ አማኞች ለውጣቸውን የሚመሰክሩ ያላመኑ ጓደኞች ስላሏቸው፡፡

3. ወደ <u>በር ጠባቂዎች</u> ሂድ፡፡

እነማን ናቸው በርጠባቂዎች?

"በር ጠባቂዎች" በሌሎች ላይ ተጽዕኖ ማሳደር የሚችሉ ወይንም ስልጣን ያለቸው ግለሰቦች ሲሆኑ የእነርሱ ወደ ጌታ መምጣት በእነርሱ ተጽዕኖ ስር ያሉ ሁሉ እንዲመጡ መንገድ ይከፍታል፡፡

ለምድን ነው እንዲህ ያሉ ሰዎችን ለመድረስ ተጨማሪ ጥረት የሚጠይቀው? እንድትወያዩበት ጥቂት መልሶችን በዚህ አስፍረናል፦

- ከፍተኛ ተጽዕኖ ያላቸው ሰዎች ልባቸውን ለክርስቶስ ለመስጠት በጣም አዝጋሚ ቢሆኑም አንድ ጊዜ ከመጡ በኋላ ግን ለወንጌል የሚኖራቸው ሚና ከፍተኛ ነው፡፡ ከእነዚህ የመጽሐፍ ቅዱስ ክፍሎች ውስጥ "በር ጠባቂዎች" እነማን እንደሆኑ ለዩ፡፡ (ሐዋ 16፡11-15፤ 17፡1-9፤ 18፡7-8)

4. ባህላዊ <u>እንቅፋቶችን</u> ከግምት ውስጥ አስገባ፡፡

ሰዎች እንዴት ነው የባህል እንቅፋትን የሚያልፉት? ለምንድን ነው እንዲህ የሚሆነው?

እንዴት ነው የምትተክለው ቤተክርስቲያን ለሚተከልበት ማህበረሰብ እንዲስማማ ማድግ የምትችለው? (1ቆሮ 9፡20-23)

5. <u>የጋራ የሚያደርጋችሁን ጉዳይ</u> አስተውል፡፡

ምን አይነት ተግባራት ለአማኙም ለማያምነውም የተለመዱ ናቸው?

## ለሞጁል 5 የሚሆን የትግበራ እቅድ (10 ደቂቃ)

ወደ ሞጁል 5 ከመሻገርህ በፊት፤ ለአዲስ ቤተክርስቲያን ተከላ እንዲያግዝህ የተዘጋጀውን እና ከዚህ በታች የቀረበውን የቤተክርስቲያን ተከላ መሪ እቅዱ በሚል ርዕስ የቀረበውን ቅጽ ተጠቅመህ መሪ እቅድህን አዘጋጅ፡፡ ከዚያም ለምትደግፍህ ቤተክርስቲያን እና መጋቢህ ወይንም በምክርና ድጋፍ ለሚያገለግልህ አገልጋይ አሳይ፡፡

# የቤተክርስቲያን ተከላ ሠፊ ዕቅድ

# ለ

---

(የተመረጠው ማህበረሰብ ስም፣ የህዝብ ብዛት፣ ወይንም መገኛ ስፍራ)

## አዘጋጅ

---

(የራስህን ስም አስገባ)

## የጸደቀው እና የሚደገፈው በ

---

(የምትደግፍህን ቤተክርስቲያን መጋቢ ወይንም በምክርና ድጋፍ የሚያገለግልህን አገልጋይ ስም)

---

(ሰነዱ በቤተክርስቲያን እና በዋና መጋቢው የተፈጋገጠበት ቀን)

## I. ጥናትና ምርምር፡- በወንጌል ሊደርሰው ስላሰብኩት ማህበረሰብ፣ ህዝብ ወይንም አካባቢ እግዚአብሔር ያሳየኝ

1. አጠቃላይ መግለጫ፡-

---

---

---

2. በጥናቱ የተገኘ ለወንጌል የሚመች አጋጣሚ እና የተከፈተ በር

3. ለወንጌል እንቅፋት የሚሆኑ ጉዳዮች እና የማሸነፊያ ስልት፡-

4. የቤተክርስቲያን ተከላ ጥሪቴን የሚያስረዱ ጠቃሚ እውነታዎች፡-

ሀ. __________

ለ. __________

ሐ. __________

ሰ. __________

ረ. __________

## II. ራዕይ ገላጭ አርፍተነገር

ራዕይ ገላጭ አርፍተነገራችሁን የሚደግፍ የመጽሐፍ ቅዱስ ክፍል፡-

## III. ተልዕኮ ገላጭ አርፍተነገር፡-

___

___

___

ተስፋሉ ገላጭ አርፍተነገራችሁን የሚደግፍ የመጽሐፍ ቅዱስ ክፍል፦

___

___

___

IV. አሴት ገላጭ አርፍተነገር

___

___

___

አሴት ገላጭ አርፍተነገራችሁን የሚደግፍ የመጽሐፍ ቅዱስ ክፍል፦

___

___

___

V. ስልታዊ እቅድ

1. ጸሎት፦

ሀ. ___

ለ. ___

መ. ___

ሰ. ___

ፈ. ___

2. ወንጌል ስርጭት፦

ሀ. ______________________________

ለ. ______________________________

ሐ. ______________________________

ሰ. ______________________________

ረ. ______________________________

3. ደቀመዝሙር ማድረግ፡-

ሀ. ______________________________

ለ. ______________________________

ሐ. ______________________________

ሰ. ______________________________

ረ. ______________________________

4. ህብረት (መሰባሰብ)፡-

ሀ. ______________________________

ለ. ______________________________

ሐ. ______________________________

ሰ. ______________________________

ረ. ______________________________

5. መሪዎችን ማደርጀት/ማብቃት፡-

ሀ. ______________________________

ለ. ______________________________

ሠ. ____________________

ሰ. ____________________

ፈ. ____________________

6. ሾምበኮ፡-

ሀ. ____________________

ለ. ____________________

ሠ. ____________________

ሰ. ____________________

ፈ. ____________________

7. ግልጋሎት

ሀ. ____________________

ለ. ____________________

ሠ. ____________________

ሰ. ____________________

ፈ. ____________________

8. ሠብዛት(ተልዕኮዎች)፡-

ሀ. ____________________

ለ. ____________________

ሠ. ____________________

ሰ. ____________________

ፈ. ______________________________

______________________ ______________________

ዋና መጋቢ ያዘጋጀው

______________________________

(የቤተክርስቲያኒቱ ተወካይ)

በዚህ ቅጽ ላይ የደጋፊ ቤተክርስቲያን እና ዋና መጋቢው ወይንም በማማከርና ድጋፍ የሚያገለግለው አገልጋይ ፊርማ መኖሩ የሚያረጋግጠው፤ ከተጠቀሰው ቀን አንስቶ ይህ የቤተክርስቲያን ተከላ እቅድ የቤተክርስቲያን ሙሉ ድጋፍ ያለው መሆኑን ነው።

የመጋቢህ፣ የምትደግፍህ ቤተክርስቲያን ወይንም በምክርና ድጋፍ የሚያገለግልህ ሰው ፊርማ እና ቀን ይመዝገብ።

የምሳ እረፍት (60 ደቂቃ)

# ክፍለትምህርት 4

# አነስተኛ የሰው ቁጥር ያለው

# የጥናት ቡድን መመስረት (60 ደቂቃ)

**ትምህርት እና ውይይት** (20 ደቂቃ)

**የአሰልጣኙ መምሪያ፡-** ከዚህ በታች ያለውን መግለጫ በመጠቀም እንዴት አነስተኛ የሰው ቁጥር ያለው የጥናት ቡድን ስለማቋቋም ተሳታፊ ሁሉ በጋራ እንዲወያዩ አድርግ። በዚያውም ተሳታፊዎች በመማሪያ መጽሐፋቸው ላይ ያለውን ክፍት ስፍራ በተገቢው ቃል እንዲሞሉ አሳስባቸው።

እነዚህን የመወያያ ነጥቦች በሚየነሱበት ወቅት እያንዳንዱ ነጥብ አነስተኛ የሰው ቁጥር ያለው የጥናት ቡድን ለማቋቋም እንደሚጠቅም ከግምት ውስጥ እንዲያስገቡ አሳስባቸው።

1. ለአዲስ ሴል ግሩፕ ተዘጋጅ።

   ሀ. ከጸሎት ቡድን (ኤፌ 6፡19፤ 1ተሰሎ 5፡25)

   ለ. ከመሪዎች ቡድን (ሉቃ 10፡1)

   መ. ለቤተክርስቲያን ተከላ ለሳሰብከው አካባቢ ጥናትና ምርምር አድርግ።

2. አዳዲስ ሰዎችን ተዋወቅ

   ሀ. ማነው አድማጭህ እንዲሆን ያሰብከው።

   ለ. እንዴት አድርገህ ከእነዚህ ሰዎች ጋር ህብረትን መመስረት ትችላለህ?

3. የአገልግሎት አካባቢ ወስን።

የምታቋቁመው አነስተኛ የሰው ቁጥር ያለው የጥናት ቡድን የት ቢሰበሰብ ትክክል ይሆናል?

4. ለመጀመሪያው የጥናት ቀን ተዘጋጅ።

ሀ. በቤተክርስቲያን ተከላ ግንባር ቀደም ሆኖ ወደ አንድ ስፍራ ለመጀመሪያ ጊዜ ወንጌልን ለማድረስ መሄድ የሚያስከትለው የተለመደ ችግር ምንድን ነው?

ለ. ይህን ችግር ለማለፍ ምን ሊደረግ ይችላል?

ሐ. አንተ በምትመራው ቡድን ውስጥ የሚገኝ አማኝ ግለሰብ፤ ቤቱን አዳዲስ ሰዎች ወደቤቱ እንዲመጡ ፈቃደኛ ሳልሆነ ሰው ምን ልትለው ትችላለህ?

አነስተኛ የሰው ቁጥር ያለው የጥናት ቡድን ማቀጃ ቅጽ (40 ደቂቃ)

**የአሰልጣኙ መምሪያ፡-** ተሳታፊዎች ይህን ቅጽ በመጠቀም ለጥናት ቡድኑ የሚሆን እቅድ እንዲያዘጋጁ አድርግ። የምትችል ከሆነ ይህን ቅጽ ኮፒ በማድረግ ለእያንዳንዳቸው በመስጠት በቡድን ሲሰሩ ኮፒ በተደረገው ላይ የመጀመሪያውን ሐሳባቸውን ካሰፈሩ በኋላ በመማሪያ መጽሐፋቸው ላይ ባለው ቅጽ ላይ ንጹህ የሆነውን ስራቸውን እንዲያሰፍሩ እድል ስጣቸው። ከተቻለ ደግሞ እነርሱ ራሳቸው ይህን ቅጽ ኮፒ በማድረግ ለሁልጊዜ የጥናት እቅድ ማውጫ ይጠቀሙበታል።

1. ከሚዘጋጀው እቅድ ውስጥ የትኛው ክሁሉ የበለጠ ቀልሎህ አገኘኸው? ለምን?

2. የትኛው ክፍልስ በጣም ከበደህ? ለምን?

3. አንተ ባለህበት ቡድን ውስጥ በዝማሬ ሰአት ዝማሬ የሚመራ ሰው ብታጣ ምን ታደርጋለህ?

4. ከጠቅላላው የጥናት ይዘት የትኛው ክሁሉም በተሻለ ይከናወናል? አስረዳ።

5. የትኛው የጥናት ክፍልስ መጥፎ ይሆናል ብለህ ትገምታለህ? አስረዳ።

# አነስተኛ የሰው ቁጥር ያለው የጥናት ቡድን ማቀጃ ቅጽ

| |
|---|
| የጥናቱ ቀን እና ጊዜ፡-______________________________. <br> የጥናቱ ቦታ እና ቤቱን የሰጠው ግለሰብ፡-______________________________. |
| **ህብረት** |
| የሻይ ሰአት፡- ______________________________. <br> ተግባራት እና ጨዋታዎች______________________________. |
| **አምልኮ** |
| የዝማሬ መሪ፡-______________________________. |
| **ጸሎት** |
| ጸሎት፡-______________________________. |
| **የመጽሐፍ ቅዱስ አሳብ ላይ መወያየት** |
| የውይይቱ መሪ፡-______________________________. <br> የጥናቱ ክፍል፡-______________________________. |
| **የአገልግሎት ራዕይን ማስቀመጥ** |
| አሳብን የማካፈል ጊዜ፡-______________________________. <br> ተግባራት፡-______________________________. |

**የአሰልጣኙ መምሪያ፡-** በመጨረሻዎቹ አስር ደቂቃዎች ካታች የቀረቡትን ጥያቄዎች በመጠቀም ስለማቀጃ ቅጹ የእቅድ አተገባበር እንደገና አስረዳ፡፡

ልናስብባቸው የሚገቡ ነገሮች፡-

- የተግባር ስልጠናህን የሚመራው ማን ነው?

- ከአንተ ጋር የሚያጠኑ እያንዳንዳቸው በማን ስር ነው ደቀመዝሙር የሚሆኑት? (እንተስ ማንን ደቀመዝሙር እያደረክ ነው?)
- እንዴት ነው የተግባር ስልጠናን በአንተ ስር የሚወስድ አገልጋይ የመሪነት ክህሎትን እንዲያዳብር ምን እያደረክ ትገኛለህ? እንዴትስ ነው አገልግሎትን ለእርሱ የምትሰጠው? እንዴትስ ነው አገልግሎትህን ንደምሳሌ የምታሳየው?
- በጥናት ቡድንህ ውስጥ ላሉት ለእያንዳንዱ ትጸልያለህ?

## ክፍለትምህርት 5

# ወንጌል ስርጭት እና የማህበረሰቡን ጉድለት መሙላት

**በግልጋሎት እና በወንጌል ስርጭት መካከል ያሉ ሶስት አይነት መስተጋብሮች የአሰልጣኙ መምሪያ፡-** በወንጌል ስርጭት እና በግልጋሎት መካከል ያለውን ሶስቱን አይነት መስተጋብሮች አስተዋውቅ፡፡ ይህን በምታደርግበት ወቅት ተሳታፊዎች በመማሪያ መጽሐፋቸው ላይ ባለው ክፍት ስፍራ ተገቢውን ቃል እንዲሞሉ አሳስብ፡፡

1. ግልጋሎት እንደ ወንጌል ስርጭት <u>ውጤት</u>፡- ወደ ክርስቶስ መመለሳችን የሌሎችን ጉድለት ስመመልከት እና ጉድለታቸውን ስመሙላት እንድንተጋ አድርጎናል፡፡

---

---

---

2. ግልጋሎት ለወንጌል ስርጭት እንደ <u>ድልድይ</u>፡- ለማህበረሰቡ በመጀመሪያ የሚሰጥ ግልጋሎት በስተመጨረሻ ሰዎች ለወንጌል ልባቸውን እንዲከፍቱ ያደርጋል፡፡

---

---

---

3. ግልጋሎት ወንጌል ስርጭትን <u>ያጅባል</u>፡- ሌሎችን እያገለገልን ስለኢየሱስ እንናገራለን፡፡

---

---

---

**የአሰልጣኙ መምሪያ፡-** ተሳታፊዎችን በሶስት ቡድን ክፈል፤ ከዚያም በምታሰለጥንበት ክፍል ውስጥ ሶስት የፖስተር መጠን ያላቸውን ወረቀቶችን በሶስት የተለያዩ ግድግዳዎች ለጥፍ፡፡ ከዚያም

የመጀመሪያው 1 "ውጤት" ብለህ ሰይመው ሁለተኛው 2 "ድልድይ" ብለህ ሰይም ሶስተኛውን 3 "አጀቢ" ብለህ ሰይመው፡፡ አንድ ቡድን በአንድ አሳብ እንዲወያዩ አድረግ፡፡ ይህን ሲያደርጉ የሚችሉትን ያህል በተሰጣቸው አሳብ ዙሪያ የወንጌል ስርጭት እና ከዚያ ጋር በተያያዘ ሲከወኑ የሚችሉ ተግባራትን ዝርዝር በወረቀቱ ላይ ያስፍሩ ይህን ሲያደርጉ ለቀጣይ ቡድን የሚሆን መጻፊያ ስፍራ መተዋቸውን አይዘንጉ፡፡ በአንዱ ርእስ አስር ደቂቃ ገደማ ከቆዩ በኋላ በቀኝ በኩል ወዳለው ቀጣይ ርዕስ በመሄድ ሌሎች የሰሩትን በማንበብ በዚያም ላይ ሌላ አስር ደቂቃ በመውሰድ እና አሳብ በመጨመር በቀኝ በኩል ወዳለው ወደ ሌላኛው  ርዕስ እንዲሄዱ ማድረግ፡፡ በእዲህ አይነት ሁኔታ ሶስቱም ቡድን ሶስቱንም ርዕስ እንዲወያዩበት ማድረግ፡፡ የተቀረውን አስር ደቂቃ ስለተግባራቱ ተጨማሪ ገለጻ ለማድረግ ተጠቀምበት፡፡ ከዚያም ተሳታፊዎች በእያንዳንዱ ወረቀት ላይ ያለውን እና ቤተክርስቲያን ለመትከል ሳሰብኩበት አካባቢ ሁኔታ ጠቃሚ ነው ያሉትን ተግባራት በመማሪያ መጽሐፋቸው ላይ እንዲገለብጡ አድርግ፡፡

# ክፍለትምህርት 6

# ከክፍሉ ሐሳብ መውሰድ የመጽሐፍ ቅዱስ ጥናት ዘዴ 3፡

# የእግዚአብሔር ቃልን መተርጎም (60 ደቂቃ)

**ክለሳ (15 ደቂቃ)**

**የአሰልጣኙ መምሪያ፡-** ከዚህ በታች በተዘረዘረው መሰረት ከዚህ በፊት ከክፍሉ ሐሳብ መውሰድ የመጽሐፍ ቅዱስ አጠናን ዘዴ ሶስቱን ደረጃዎች የምንጠቀምበትን ሂደት እንዲያስታውሱ ጠይቃቸው፡፡ (ከሞጁል 1)

1. ምልከታ- ምን ይላል?

2. መተርጎም- ምን ማለት ነው?

3. ማዛመድ- ምን ማድረግ ይጠበቅብኛል?

**የአሰልጣኙ መምሪያ፡-** ከዚህ በታች የቀረበውን (ከሞጁል 2) ዝርዝር በመመልከት ሂደት ውስጥ የምንከተላቸውን ደረጃዎች እንዲያስታውሱ ጠይቅ፡፡

1. ክፍሉ ምን እንደሚል ለማወቅ በጥንቃቄ ለመመልከት ተዘጋጅ፡፡

2. በቂ ጊዜ ውሰድ

3. መጽሐፍ ቅዱሳዊ አውዱን ተመልከት (ሁኔታውን) የሚከተሉትን አመዛዝን፡-

4. የጥናት ክፍሉን አደረጃጀት መርምር

5. የምርመራ ጥያቄዎችን ስለክፍሉ ጠይቅ

ያጠኑትን ማካፈል (15 ደቂቃ)

**የአሰልጣኙ መምሪያ፡-** የማስተማሪያ ይዘቱን በመጠቀም ተሳታፊዎች ከዚህ በታች ከክፍሉ ሐሳብ በመውሰድ የመጽሐፍ ቅዱስ አጠናን ዘዴ፤ ስለ መተርጎም የቀረበውን ዝርዝር እንዲያሟሉ አበረታታቸው።

1. መተርጎም - ከመልዕክቱ ሐሳብ የመውሰድ አጠናን ዘዴ ሁለተኛው ደረጃ

2. ከክፍሉ ሐሳብ የመውሰድ ሂደት

   - በምልከታ ወቅት ያገኘሃቸው ቁልፍ እውነታዎች ላይ ያለህን ሐሳ ግለጥ
   - የጸሐፊውን ዋና ሐሳብ ለይተህ አውጣ
   - በክፍሉ ውስጥ ያለውን የሐሳብ ፍሰት ለይተህ አውጣ

3. የመተርጎም መሰረታዊ ህጋት

- መጽሐፍ ቅዱስን የመተርጎም አጠቃላይ መርሆች
  - ➢ መጽሐፍ ቅዱስ ባለሙሉ ስልጣን የእግዚአብሔር ቃል ነው።
  - ➢ መጽሐፍ ቅዱስ ራሱ ለራሱ ከሁሉ የተሻለ ተርጓሚ ነው፤ ስለእግዚአብሔር ባህርይ የሚገልጥ ስለሆነ።
  - ➢ ቃለ እግዚአብሔርን ለመረዳት የሚያድግን እምነት እና መንፈስ ቅዱስ አስፈላጊ ናቸው።
  - ➢ ታሪክን፣ ተግባራትን፣ አመለካከቶችን፣ የግል ልምምድን ወ.ዘ.ተ...መተርጎም ያለብህ በመጽሐፍ ቅዱስ ብቻ ነው።
  - ➢ የቃለ እግዚአብሔር ዋና አላማ እውቀታችንን መጨመር ሳይሆን ሕይወታችንን መለወጥ ነው።
  - ➢ እያንዳንዱ ክርስቲያን በመንፈስ ቅዱስ በመታገዝ የእግዚአብሔርን ቃል የመመርመር እና የመተርጎም መብት፣ ኃላፊነት እና እድል አለው።
- መጽሐፍ ቅዱስን የመተርጎም ሰዋሰዋዊ፣ ታሪካዊ እና ስነመለኮታዊ መርሆች

- ቃላትን መተርጎም ያለባቸው በጸሐፊው ታሪካዊ እና ባህላዊ አውድ ብቻ ነው፡፡ ሁልጊዜም ማሰብ የሚገባን የመጽሐፉ ተደራሲያን እንዴት እንደተረዱት እና ለመልዕክቱ ምላሽ እንደሰጡ ማሰብ ነው፡፡
- አንድ ክፍል የሚያስተምረውን ስነመለኮታዊ እውነት ለመረዳት ከመሞከራችን በፊት ሰዋሰዋዊ ይዘቱን መረዳት ቀዳሚ ተግባር መሆን ይገባዋል፡፡
- ተምሳሌታዊ ቃላት አንድ ዋና ትርጉም ብቻ እንዳላቸው የታወቀ ነው፡፡ በአንድ ተምሳሌታዊ ምልክት ወይንም አሳብ ብዙ ትርጉም አዳለው በማሰብ በብዙ ትርጓሜ አንዱን ክፍል ማንበብ ተገቢ አይደለም፡፡
- መጽሐፍ ቅዱስ ግልጽ አድርጎ ካስቀመጠው በላይ አንተ ግልጽ የምታደርገው ምንም የለም፡፡ የራስህን አሳብ ሆነ የቤተክርስቲያንን ባህል በቃሉ ላይ አትጨምር፤ ምክንያቱም ሲቀይ አንተም ሆንክ ሌሎች ይህ አሳብ እና ባህል ቃለ እግዚአብሔር እንደሆነ ልታምኑ ትችላላችሁ፡፡

- ልናስወግዳቸው የሚገቡ የተለመዱ ስህተቶች
  - መስፈንጠሪያ፡- ከአንዱ ክፍል ወደ ሌላው ክፍል በመዝለል ልናስረዳ ያሰብነውን አሳብ ብቻ ተከትሉ መጽሐፍ ቅዱስን ማንበብ፡፡
  - ተምሳሌት/አሊጎሪ፡- መጽሐፍ ቅዱስ በግልጥ ያስቀመጠውን ትርጉም በመተው የተሰወረ ትርጉም እንዳለ ማሰብ እና መፈለግ፡፡
  - እየጨመረ የሚሄድን መገለጥ ችላ ማለት፡- እየጨመረ የሚሄድ መገለጥ የመጽሐፍ ቅዱስ ባህሪ እንደሆነ ችላ ማለት፡፡

አነስተኛ የሰው ቁጥር ያለው የጥናት ቡድንን በተግባር ማዋል (30 ደቂቃ)

የአሰልጣኙ መምሪያ፡- ተሳታፊዎችን በቡድን በመመደብ ከዚህ በታች የቀረበውን የመተርጎም ልምምድ እንዲያጠናቅቁ አድርግ፡፡ ከእያንዳንዱ ቡድን አንድ ፈቃደኛ የሆነ ሰው አስጠኚ በመሆን እንዲያገለግል አድርግ፡፡ የዚህ ፈቃደኛ አስጠኚ ተግባር የጥናቱን ሂደት ማሳለጥ ብቻ ነው፡፡ ጊዜ ካለህ ይህን ክፍል ብትከልሱላቸው የተሻለ ነው፡፡

ስቡድኑ የተሰጠ መምሪያ፡- በሞጁል 2 ላይ በት.ሴር 1 ዙሪያ ያደረጋችሁትን ምልከታ ከመጽሐፋችሁ ደግማችሁ አስታውሱ፡፡ ጊዜ የሚፈቅድላችሁ ከሆነ የመተርጎሙንም ሂደት ብትከውኑ መልካም ነው፡፡ ከዚህ በታች ስመምሪያነት የሚያገለግል ቅጽ ቀርቦላችኋል፡፡

1. የመጽሐፉን ቁልፍ ምልከታ አግኝ

2. ዋናውን ነጥብ ዘርዝር

3. የአሳብ ፍሰቱን ግለጥ

4. በአንዳንድ የ"ትርጉም" ጥያቄዎች ላይ አሳብህን ግለጥ፡፡

ከላይ ያሉትን አርፍተነገሮች ስትሰራ ስለክፍሉ ትርጉም የቀረቡትን ጥያቄዎች ከግምት ውስጥ ማስገባት ጠቃሚ ይሆናል፡፡ እንደውም የተሻሉ ወይንም የበለጡ ጥያቄዎችን አስብ፤ እነዚህ ሂደቱን እንድታስብ ብቻ የቀረቡ ናቸው፡፡

ቁጥር 5

እግዚአብሔር ኤርሚያስን "ያውቀዋል" ማለት ምን ማለት ነው? "ለይቼሃለሁ" ማለትስ ምን ማለት ነው?

"ከማኅፀንም ሳትወጣ ቀድሼሃለሁ" ይህ አርፍተነገር ምን ያመለክታል?

ቁጥር 6

ኤርሚያስ ራሱን "ብላቴና/ትንሽ ልጅ" ነኝ እንዲል ያደረገው ምን ሊሆን ይችላል?

ኤርሚያስ እንዲህ ብሎ እንዲመልስ ያደረገው ምንድን ነው ብለህ ታስባለህ?

ቁጥር 7

በዚህ ቁጥር ካየኸው ተነስተህ ከእግዚአብሔር የሆነን ጥሪ እንዴት ትገልጸዋለህ? ከዚህ በታች ካለው ጥያቄ፤ እግዚአብሔር ለኤርሚያስ የሰጠውን ምላሽ በማየት ስለእግዚአብሔር እና ስለባህርይው ምን ልንማር እንችላለን?

ቁጥር 8

ኤርሚያስ ወደፊት ስለሚያገለግላቸው ሰዎች እና ለአገልግሎቱ ስለሚሰጡት ምላሽ የእግዚአብሔር ቃል ምን ይላል?

ኤርሚያስ ጠላቶቹን እንዲጋፈጥ የሚያነሳሳው ነገር ለስ?

ቁጥር 9

እንዴት ነበር እግዚአብሔር ቃሉን በኤርሚያስ ውስጥ "ያኖረው"?

ቁጥር 10

"*ትነቅልና ታፈርስ ዘንድ፥ ታጠፋና ትገለብጥ ዘንድ፥ ትሠራና ትተክል ዘንድ*" እነዚህ ሐረጎች ምን ማለት ናቸው ብለህ ታስባለህ?

የእግዚአብሔርን እቅድ ተከትሎ ለመኖር የሚያስችል፣ በኤርሚያስ ውስጥ የሚገኝ ምን አይነት ባህርይ አለ ብለህ ታስባለህ?

ቁጥር 12

እግዚአብሔር በጠራቸው ሰዎች አገልግሎት ውስጥ እግዚአብሔር በእያንዳንዱ እንቅስቃሴ አብሮነቱ እንደሚሰራ የሚያሳይ ምን አይነት መርህ ከዚህ ቁጥር ለሳብ እናገኛለን?

ቁጥር 16

እግዚአብሔር የእኔ የሚለው ህዝብ ላይ ሲፈርድ ስትመለከት ፤ ስለእግዚአብሔር ባህርይ ከዚህ ቁጥር ምን ትረዳለህ?

እግዚአብሔር ለህዝቡ ሲያደርግ ባቀደው ጉዳይ የሚገባ/ምክንያታዊ ነው ብለህ ታስባለህ? ለምን?

ቁጥር 17

የኤርሚያስ "ዝግጅት" አንዱ ክፍል ምን ሊሆን ይችላል?

እግዚአብሔር ከዚህ ቀደም በሌላ ቁጥር ላይ የተናገረውን ደግሞ የተናገረው ምንድን ነው (ቁጥር 8)?

ቁጥር 18

ከዚህ ቀጥሎ የቀረቡት ሐረጎች ትርጉም ምንድን ነው "እንደ ተመሸገ ከተማ እንደ ብረትም ዓምድ እንደ ናስም ቅጥር "?

ለምንድን ነው በቁጥር 18 ላይ ያሉት ሰዎች ኤርሚያስን እና መልእክቱን የሚቃወሙት?

በዚህስ ዘመን እግዚአብሔር ከእርሱ ጋር ይስማሙና ይቆሙ ዘንድ ህዝቡን የሚያበረታታው?

ቁጥር 19

እግዚአብሔር ለጠራቸው ሰዎች ስለሚያሳየው ባህርይ እና ተግባር ይህ ክፍል ምን ይነግረናል?

ቀጣዩ ምንድን ነው?

**የአሰልጣኙ መምሪያ፡-**

- ለሞጁል 5 የተዘጋጁን ሁለቱን የትግበራ እቅዶች ከልሱ።
- ለቤተክርስቲያን ተከላ የምናካሂደው ወንጌል ስርጭት አምስቱን መርሆች ተሳታፊዎች እንዲያስታውሱ (ሞጁል 3)

- በግልጋሎት እና ወንጌል ስርጭት መካከል ያሉትን ሶስት ግንኙነቶች እንዲያስታውሱ ተሳታፊዎችን ጠይቅ (ክፍለትምህርት 5ን ተመልከት)፡፡
- ተሳታፊዎች እንደ ቤተክርስቲያን ተከላ አገልጋይ ከዚህ ስልጠና ያገኙትን አነቃቂ፣ አበረታች ወይንም ስለሌ የሚያነሳሳ ትምህርት ካለ ለተሳታፊዎች እንዲያቀርቡ እድል ስጥ፡፡
- ተሳታፊዎች ለዚህ ወር የሚሆን የቤተክርስቲያን ተከላ እቅድ ያውጡ (ከታች ያለውን ሰንጠረዥ ተመልከት)፡፡
- የአምልኮ መዝሙር ከዘመራችሁ በኋላ በጸሎትና በሩሌ ለቀጣዩ የቤተክርስቲያን ተከላ ተግባር ተንቀሳቀሱ፡፡

ወደሚቀጥለው ሞጁል ከመሻገራችሁ በፊት የሚከተሉትን ተግባራት እንድትፈጽሙ እናበረታታችኋለን፡፡

- ➢ ከዚህ በፊት የማታውቃቸውን አስር ሰዎች ተዋወቅ
- ➢ ለአምስት ሰዎች ወንጌል ስበክ
- ➢ አንድ አዲስ አነስተኛ የሰው ቁጥር ያለው የጥናት ቡድን አቋቁም

### ለሞጁል 5 የሚሆን የትግበራ እቅድ፡- የመቅጣጠሪያ ቅጽ

- ➢ ጽድቅን የተመለከተ የመጽሐፍ ቅዱስ ጥናት በማድረግ ተሳታፊዎች ራሳቸውን የጽድቅ ትርጓሜን ያውጡ (ክፍለትምህርት 1)፡፡
- ➢ የቤተክርስቲያን ተከላ መሪ ዕቅዱን ሙሉ (ክፍለትምህርት 3ን ተመልከት)

| ለዚህ ወር የሚሆን የቤተክርስቲያን ተከላ ግብ | |
|---|---|
| **ግለሰቦች** | |
| የተዋወቅናቸው ሰዎች | እባክዎን በቁጥር ያስቀምጡ |
| ወደጌታ በቅርብ የመጡ | እባክዎን በቁጥር ያስቀምጡ |
| በቅርብ የውሃ ጥምቀት የወሰዱ | እባክዎን በቁጥር ያስቀምጡ |
| በስልጠና ላይ ያሉ መሪዎች | እባክዎን በቁጥር ያስቀምጡ |
| **ትናንሽ ቡድኖች** | |
| አዳዲስ ትናንሽ ቡድኖች | እባክዎን በቁጥር ያስቀምጡ |
| በትናንሽ ቡድኖች ውስጥ የሚሳተፉ አባላት | እባክዎን በቁጥር ያስቀምጡ |
| በጥናት ቡድኖች ውስጥ ያሉ መሪዎች | እባክዎን በቁጥር ያስቀምጡ |